# ከጀርመን - በርሊን የኢትዮጵያ ኤምባሲ የቆንስላ አገልግሎት ለማግኘት የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ - ሁኔታዎች

## ሀ) አጠቃላይ

- ለማንኛውም የቆንስላ አገልግሎት የሚያስፈልግ ባዮሜትሪክ ፎቶግራፍ ሲነሱ 3 x 4 ሴ.ሜ ስፋት ያለው 4 ፎቶዎች ማቅረብ የሚገባዎ ሲሆን የሰውነትዎን ምስል በመቀስ መከርከም የሌለበት፣ ከጀርባው /Background/ ነጣ ያለ፣ ሁለቱም ጆሮዎችዎ የሚታዩ መሆን ይገባዋል::
- አዲሱ ዲጂታል ፓስፖርት በኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ (አዲስ አበባ) ስለሚዘጋጅ የአንድ ወር ተኩል ጊዜ ሊወስድ ይችላል::
- ከአዲሱ ፓስፖርት በስተቀር በአካል በኤምባሲው እስከተገኙ ድረስ ከአንድ ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የቆንስላ አገልግሎቱን ማግኘት ይችላሉ::
- በአካል መገኘት የማይችሉ ከሆነና የአገልግሎት ጥያቄዎን በፖስታ ካቀረቡ አገልግሎቱ የአንድ ሳምንት ጊዜ ይወስዳል::
- በፖስታ ከሆነ ቴምብር የተለጠፈበትና የላኪ አድራሻ (አድራሻዎ) በትክክል የተፃፈበት መልሶ መላኪያ ፖስታ መላክ ይኖርብዎታል::

የአገልግሎት ክፍያ ለመፈፀም፣

**1) በጀርመን ውስጥ**

**Commerzbank Berlin**
**Account No. - 2673978**
**BLZ – 10040000**

**2) ከጀርመን ውጭ (ከፖላንድ፤ ቼክና ስሎቫኪያ ብቻ)**

**Commerzbank Berlin**
**IBAN: DE31 1004 0000 0267397800**
**Swift Code (BIC): COBADEFFXXX**

በምንሰጠው አገልግሎት ቅሬታና አስተያየት ካለዎት በድረ-ገፃችን በተዘጋጀው የአስተያየት መስጫ ቅጽ ላይ በመሙላት እንዲያቀርቡ በአክብሮት እንጠይቃለን::

ለ) ዝርዝር መረጃ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | በተገል ጋዮች መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች | ክፍያ | ተጨማሪ ማብራሪያ | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | *ፓስፖርት*<br>*1.1 አዲስ - ለአዋቂዎች* | • የፓስፖርት መጠየቂያ ሁለት ቅጂ ቅፅ መሙላት፣<br>• በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የልደት ሰርተፊኬት፣ወይም ወደ ጀርመን የገቡበት ፓስፖርት ማቅረብ:<br>• በአካል በመቅረብ አሻራ መስጠት፣<br>• 4 ጉርድ ባዮሜትሪክ ፎቶግራፍ መጠናቸው 3x4 ሴ..ሜ የሆነ መቅረብ፣<br>• ከሚኖሩበት ሀገር የመኖሪያ ፈቃድ ማቅረብ አለበት:: | 42.50 ዩሮ<br><br>21.25ዩሮ (ለተማሪ) | • ተማሪዎች ከት/ቤታቸው የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::<br>• በአካል በመቅረብ አሻራ መስጠት የማይችሉ ከሆነ ሚሲዮኑ ከተወከለባቸው አገሮች (ጀርመን፣ ቼክ ሪፐብሊክ፣ ፖላንድ እና ስሎቫክ) ላሉ የክብር ቆንስላዎች ወይም ለአካባቢ ፖሊስ መስጠትና በፓብሊክ ኖታሪ እንዲሁም በሀገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር በማረጋገጥ መላክ::<br>• በአዲሱ ዲጂታል ፓስፖርት አሰራር መሰረት ህፃናት የራሳቸው ፓስፖርት ይይዛሉ እንጂ በወላጅ ፓስፖርት ላይ አይመዘገቡም:: | 6 ሳምንት |
| | *1.2 በውጭ ሀገር ለተወለዱ ህፃናት* | • የፓስፖርት መጠየቂያ ሁለት ቅጂ ቅፅ መሙላት፣<br>• የሕፃን የልደት ምስክር ወረቀት፣<br>• ህፃኑ/ህፃኗ ፓስፖርት እንዲሰጠው/እንዲሰጣት የአባትና እናት ስምምነት ያለበት ማመልከቻ፣<br>• የወላጆች ፓስፖርት ኮፒ፣<br>• ህፃኑ/ህፃኗ የሌላ ሀገር ዜግነት ያለመውሰዳቸው ከሚመለከተው ክፍል የተሰጠ ማስረጃ፣<br>• 4 ጉርድ ባዮሜትሪክ ፎቶግራፍ መጠናቸው 3x4 ሴ.ሜ የሆነ ማቅረብ ያስፈልጋል:: | | | |

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | በተገልጋዮች መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች | ክፍያ | ተጨማሪ ማብራሪያ | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *1.3 ገፆቹ ወይም የአገልግሎት ጊዜው ያለቀ ወይም የተበላሸ ፓስፖርት ለመቀየር* | • የፓስፖርት ለውጥ መጠየቂያ ሁለት ቅጂ ቅፅ መሙላት፣<br>• ገፆቹ ወይም የአገልግሎት ጊዜው ያለቀ ወይም የተበላሸው ፓስፖርት፣<br>• የመኖሪያ ፈቃድ ኮፒ፣<br>• 4 ጉርድ ባዮሜትሪክ ፎቶግራፍ መጠናቸው 3x4 ሴ.ሜ የሆነ ማቅረብ ያስፈልጋል:: | 42.50 ዩሮ<br>21.25 ዩሮ (ለተማሪ) | የሚቀየረው ፓስፖርት አዲሱና በማሽን የሚነበበው ከሆነ አሻራ መስጠት አያስፈልግም:: ይሁን እንጂ አመልካቾች በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል። | 6 ሳምንት |
| | *1.4 በጠፉ ምትክ* | • ስለ መጥፋቱ ለፖሊስ አመልክተው የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ፣<br>• ከጀርመን የውጭ ዜጎች ጉዳይ ክፍል የተሰጠ መኖሪያ ፈቃድ ወይም የአኗኗርዎን ሁኔታ የሚገልፅ ማረጋገጫ ደብዳቤ ማቅረብ፣<br>• የፓስፖርት መጠየቂያ ሁለት ቅጂ ቅፅ መሙላት፣<br>• በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የልደት ሰርተፊኬት ማቅረብ፣<br>• በአካል በመቅረብ አሻራ መስጠት፣<br>• 4 ጉርድ ባዮሜትሪክ ፎቶግራፍ መጠናቸው 3x4 ሴ.ሜ የሆነ ማቅረብ ያስፈልጋል:: | 51 ዩሮ | • ስለመጥፋቱ ለአካባቢ ፖሊስ ያሳወቁ ዕለት በተመሳሳይ ለኤምባሲው ቆንስላ ክፍል በደብዳቤ ማሳወቅ፣<br>• የጠፋው ፓስፖርት ሊገኝ ስለሚችል በፖሊስ ካስመዘገቡ በኋላ እስከ ሁለት ሳምንት መቆየት ያስፈልጋል:: | 6 ሳምንት |
| 2 | *የይለፍ ሰነድ (ሊሴ-ፓሴ)* | • በሁለት ቅጂ ማመልከቻ ቅፅ መሙላት፣<br>• የኢትዮጵያዊነት ማረጋገጫ ቅፅ መሙላት፣<br>• 4 ጉርድ ባዮሜትሪክ ፎቶግራፍ መጠናቸው 3x4 ሴ.ሜ የሆነ ማቅረብ ያስፈልጋል:: | 17 ዩሮ | • ሰነዱ የሚያገለግለው ለአንድ ጊዜ መውጫ ብቻ ነው::<br>• በእስር ሳይሆን በፍላጎት ወደ ሀገር ለመመለስ የሚፈልጉ ከሆነ በኤምባሲው በመገኘት ማመልከት ያስፈልጋል:: | 45 ደቂቃ |

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | በተገልጋዮች መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች | ክፍያ | ተጨማሪ ማብራሪያ | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | *በትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ*<br>*3-1 አዲስ* | • በሁለት ቅጂ የማመልከቻ ቅፅ መሙላት፣<br>• ዜግነት ካገኙበት ሀገር የተሰጠ የፀና ፓስፖርት ማቅረብ፣<br>• የኢትዮጵያ ተወላጅነት ማስረጃ (የልደት ሰርተፊኬት፣ ይገለገሉበት የነበረው የድሮ የኢትዮጵያ ፓስፖርት ኮፒ፤ የትምህርት ማስረጃ ወዘተ)፣<br>• 4 ጉርድ ፎቶግራፍ መጠናቸው 2x3 ሴ.ሜ የሆነ መቅረብ አለበት::<br><br><u>በተጨማሪ</u><br>ሀ) ለውጭ ሀገር ዜጋ ባለቤትዎ<br>• በሁለት ቅጂ ማመልከቻ ቅፅ መሙላት፣<br>• የጋብቻ ሰርቲፊኬት ማቅረብ፣<br>• የአመልካች የትውልድ መታወቂያ ማቅረብ፣<br>ለ) ልጆችን ለማካተት<br>• ዕድሚያቸው ከ18 ዓመት በታች መሆናቸውን የሚያሳይ የልደት ሰርቲፊኬት ማቅረብ፣<br>• የአባት ወይም የእናት ስምምነት ያለበት ማመልከቻ ከፓስፖርት ኮፒ ጋር ማቅረብ ይገባል:: | 100 የአሜሪካ ዶላር | ልጆችን ለማካተት ክፍያ የለውም:: 18 ዓመት ሲሞላቸው ግን የራሳቸው መታወቂያ ሊኖራቸው ይገባል:: | ማመልከቻዎን ካቀረቡ በኋላ በሚሰጥዎት ቀን ቀጠሮ መሰረት ይስተናገዳሉ፣ |
| | *3-2 ዕድሳት* | • የዕድሳት ቅፅ መሙላት፣<br>• ኦሪጅናል የትውልድ መታወቂያ ማቅረብ፣<br>• የፓስፖርት ኮፒ ማቅረብ ያስፈልጋል:: | 40 የአሜሪካ ዶላር | • በአካል መገኘት/መቅረብ ግዴታ አይደለም:: | 1 ሰዓት |

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | በተገልጋዮች መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች | ክፍያ | ተጨማሪ ማብራሪያ | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *3-3 በጠፋ ወይም በተበላሸ ምትክ* | • መጥፋቱን ያመለከቱበት ከፖሊስ የተሠጠ ማስረጃ ከማመልከቻ ጋር አያይዞ ማቅረብ ያስፈልጋል:: | 60 የአሜሪካ ዶላር | • የጠፋው መታወቂያ ሊገኝ ስለሚችል በፖሊስ ካስመዘገቡ በኂላ እስከ ሁለት ሳምንት መቆየት፣<br>• ለፖሊስ ያመለከቱ ዕለት ወድያውኑ በተመሳሳይ ለኤምባሲ ማሳወቅ ያስፈልጋል:: | 1 ሰዓት |
| 4 | *ውክልና መስጠት* | • በማመልከቻ መጠየቅ፣<br>• በኤምባሲው በተዘጋጀው የውክልና መስጫ ቅፅ መሰረት ወይም በራስዎ የተዘጋጀ የሚፈለገውን የውክልና ዓይነትዝርዝር በሁለት ቅጂ ማቅረብ፣<br>• ኦሪጅናል የኢትዮጵያ ፓስፖርት/ በትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ/የስደተኛ መታወቂያ/የጉዞ ሰነድ ማቅረብ ያስፈልጋል:: | 52.70 ዩሮ | • ቀጠሮ በቅደሚያ ይዘው ወደ ኤምባሲ በአካል መቅረብ፣<br>• ለተለያዩ የውክልና ዓይነቶች ጠቀሜታ የሚውሉ በቆንስላ ክፍሉ የተዘጋጁ የውክልና መስጫ ቅፆች ከማስተናገጃ ቦታ/ ከድረ-ገፅ ማግኘት ይችላሉ:: | 1 ሰዓት |
| 5 | *ሰነድ ማረጋገጥ (የትምህርት: የልደት: የጋብቻ: የፍቺ: ያላገቡ)* | • ጥያቄውን በማመልከቻ በዝርዝር ማስፈር፣<br>• ፓስፖርትና የመኖሪያ ፈቃድ ኮፒ፣ ሰነዱን በ Public Notary እና Distric Court አረጋግጦ፣(ፖላንድ ስሎቫክና ቼክ ሪፐብሊክ ነዋሪ ለሆኑ ሰነዱን በየአገሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አረጋግጦ) ማቅረብ አስፈላጊ ነው:: | 52.70 ዩሮ | | 45 ደቂቃ |
| 6 | *በህይወት የሚኖሩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ* | • ጥያቄውን በማመልከቻ ማቅረብ፣ ፓስፖርት በአካል ይዞ መቅረብ፣ አገልግሎቱን በአካል ቀርበና ፈርሞ መጠየቅ ያስፈልጋል:: | ከክፍያ ነፃ | | 45 ደቂቃ |

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | በተገልጋዮች መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች | ክፍያ | ተጨማሪ ማብራሪያ | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|
| 7 | *ህይወቱ ያለፈ ዜጋን አስከሬን ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ* | • የሟች ሰነድ (ፓስፖርት፡ የመኖሪያ ፈቃድ ኮፒ)፣<br>• የህልፈት ሰርተፊኬት (death certificate) ከማዘጋጃ ቤት ወይም ከሆስፒታል የተሰጠ፣<br>የአሟሟት ሁኔታ (በአደጋ ወይም በህመም ወዘተ.) ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የፖሊስ ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል:: | ከክፍያ ነፃ | | 45 ደቂቃ |
| 8 | *ከወንጀል ነፃ ማረጋገጫ* | • ፍላጎትዎን ከነምክንያቱ በማመልከቻ ማስፈር፣<br>• 2 ፎቶግራፎች ነጣ ያለ ጀርባ /Background/ ያላቸው ተነስተው ማቅረብ፣<br>• ፓስፖርት በአካል ይዞ በመቅረብ አሻራውን መስጠት፣<br>• የሚኖሩት በጉዞ ሰነድ ከሆነ 3 ኢትዮጵያውያን ምስክሮችና የመስካሪዎችን ፓስፖርት ኮፒ ማቅረብ ያስፈልጋል:: | ከክፍያ ነፃ | ከወንጀል ነፃ ስለመሆንዎ ማረጋገጫ የሚሰጠው አዲስ-አበባ የሚገኘው የፌደራል ፖሊስ ፎረንሲክ ክፍል በመሆኑ ጉዳይዎን ተከታትሎ የሚያስፈፅምልዎት ሰው መወከልና ለዚሁ አገልግሎት የሚያስፈልግ ማስረጃና ክፍያ በተራ ቁጥር 4 እንደተዘረዘረው ማሟላት ያስፈልጋል:: | 1 ሰዓት |
| 9 | *ጋብቻ ለመፈፀም* | • በሁለቱም ተጋቢዎችና ሁለት ሁለት ምስክሮቻቸው የተፃፈና የተፈረመ የጋብቻ መረጃ የምስክር ወረቀት መጠየቂያ ቅፅ በመሙላት ማቅረብ፣<br>• ይኖሩበት ከነበረ ቀበሌ የተሰጠና በኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር የተረጋገጠ ያላገባ/ች ማረጋገጫ ማቅረብ፣<br>• የተጋቢዎችና የአራቱም ምስክሮች ፓስፖርትና የመኖሪያ ፈቃድ ኮፒ ማቅረብ<br>• የተጋቢዎች ሶስት ሶስት 3 በ 4 ሴ.ሜ ስፋት ያለው ፎቶግራፍ ማቅረብ ያስፈልጋል:: | | • ጋብቻ በአካል በመቅረብ የሚፈፀም እንጂ በውክልና አይቻልም፣ ተጋቢ ፍላጎታቸውን ከነምክንያቱ በማመልከቻ ማስፈር እና<br>• ተጋቢዎች የሚያቀርቡት ያላገባ/ያላገባች ማስረጃ ከተሰጠበት ጊዜ እስከ ስድስት ወር ድረስ የሚያገለግል ይሆናል፣ ጊዜው ከዚያ ካለፈ የታደሰ ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል:: | 1 ሰዓት |